Seattle Department of Education & Early Learning

# የሲያትል ከተማ የጣፋጭ መጠጥ ታክስ (SBT)
# ከቅድመ ወሊድ እስከ ሶስት ዓመት (PN-3) የማህበረሰብ የገንዘብ ስጦታ ፕሮግራም
# ለውሳኔ የቀረበ ሀሳብ ጥያቄ (RFP) ማጠቃለያ ተጓዳኝ

## መግቢያ

የትምህርት እና የቅድመ ትምህርት መማሪያ መምሪያ (DEEL) ከቅድመ ወሊድ እስከ ሶስት አመት ባለው ጊዜ ውስጥ ለግለሰቦች የጤና እና የትምህርት ውጤቶችን ለማሻሻል አገልግሎት ለመስጠት ፍላጎት ያላቸውን ማህበረሰብን መሠረት ላደረጉ ድርጅቶች (CBOs) ለእቅድ ሀሳቦችን እንዲያቀርቡ እየጠየቀ ነው።

ለ2024-2026 ለዚህ መዋዕለ ንዋይ በግምት $1.49 ሚሊዮን ዶላር አለ። ብቁ የሆኑ ተቋሞች እስከ ሁለት ዓመት ውስጥ በድምሩ $298,000.00 ዶላር የሚሆን በእያንዳንዱ ዓመት $149,000.00 ዶላር የሚጠይቅ አንድ የእቅድ ሀሳብ ማቅረብ ይችላሉ። የገንዘብ ድጋፍ በሲያትል ከተማ የትምህርት እና የቅድመ ትምህርት መማሪያ መምሪያ (DEEL) በሚተዳደረው ሂደት በዚህ ለውሳኔ የቀረበ ሀሳብ ጥያቄ (RFP) በኩል ይሸለማል። ይህ PN-3 ለማህበረሰብ የስጦታ ገንዘብ ለውሳኔ የቀረበ ሀሳብ ጥያቄ (RFP) በሶስት የትኩረት መስኮች ለውሳኔ የቀረቡ ሀሳቦችን ይሻል:-

1. ጤናማ እና ፍትሃዊ እኩልነት ያላቸው ልደቶች
2. የወላጅ ጤና እና ስነ ስሜታዊነት ደህንነት
3. ልጅ ማሳደግ እና የምላሽ ሰጪነት እንክብካቤ

DEEL የተለየ ፍላጎት የሚሰጣቸውን እንደ የቀለም ማህበረሰቦች፣ አዲስ ሰፋሪዎች፣ ስደተኞች፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተብለው የተገለጹ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ህዝቦች ለመድረስ፣ በሲያትል ከተማ ውስጥ ለመውለድ የሚጠባበቁ ወላጆችን፣ ተንከባካቢዎችን እና/ወይም አሳዳጊዎችን ለማገልገል ተልዕኮ ያላቸውን ማህበረሰብን መሠረት ላደረጉ ድርጅቶች (CBOs) የገንዘብ ድጋፍ ቅድሚያ በመስጠት ላይ ነው። የተሳካላቸው ለውሳኔ የቀረቡ ሀሳቦች የሁለት አመት የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ።

## ብቁነት እና የገንዘብ ድጋፍ

በዚህ RFP በኩል የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ለመሆን የውሳኔ ሀሳብ አቅራቢዎች ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ መሆን አለባቸው:

- ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት (ወይም በገንዘብ ማግኘት በአንድ ድርጅት የተደገፈ) (ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ ወይም እምነትን መሰረት ያደረጉ ድርጅቶችን ጨምሮ) የ 501(c)3 ደረጃ ያለው
- እንደ የማህበረሰብ ተራድኦዎች፣ ጥምረቶች እና/ወይም ሌሎች የጠበቀ ዝምድና ቡድኖች ያሉ፣ እንደ ለትርፍ ያልተቋቋመ ተብሎ ሕጋዊ ያልሆነ የማህበረሰብ ድርጅት ወይም ኅብረት የመምሪያውን አስፈላጊ የውል ስምምነት መስፈርቶች በማሟላት በገንዘብ የተደገፉ መሆናቸው ተለይቶ መታወቅ አለባቸው
- ጎሳዎች እና የጎሳ ድርጅቶች

በተጨማሪም፣ ለውሳኔ የቀረቡ ሀሳቦች በሲያትል ከተማ ገደቦች ውስጥ ለሚኖሩ ተሳታፊዎች አገልግሎት መስጠት አለባቸው።

Seattle Department of Education & Early Learning

ይህ የገንዘብ ድጋፍ አስቀድሞ በሌሎች የህዝብ ዶላር ለሚደገፉ አገልግሎቶች ጥቅም ላይ እንዲውል የታሰበ አይደለም።

ለዚህ የገንዘብ ድጋፍ ዕድል ብቁ ያልሆኑ ፕሮጀክቶች የሚከተሉትን ለውሳኔ የቀረቡ ሀሳቦች ያካትታሉ:

- ፈቃድ ለተሰጠው የልጅ እንክብካቤ ሥራ ጥራት ያለው ድጋፎችን ወይም ድጎማዎችን ማቅረብ
- የአንድ ድርጅት አጠቃላይ ተግባራትን በመደገፍ ላይ ብቻ ማተኮር
- ከቅድመ-ወሊድ-እስከ-ሶስት-እድሜ ላይ ያለ ማዕከላዊ ትኩረት መሆናቸው
- በፖለቲካ ባለስልጣን ማግባባት ላይ ያተኮረ
- **በአሁኑ ጊዜ ከ2023-2025 የገንዘብ ድጋፍ የተሰጣቸው PN3 የማህበረሰብ የገንዘብ ስጦታ አጋሮች**

## የእንቅስቃሴዎች መርሃ ግብር

| ክስተት | ዕለተ ቀን/ሰዓት |
|---|---|
| **ለውሳኔ የቀረበ ሀሳብ ጥያቄ (RFP) ይከፈታል** | **መጋቢት 28 ቀን 2024** |
| **የRFP መረጃ ክፍለ ጊዜ (ቀድሞ-የተቀዳ)** | **መጋቢት 28 ቀን 2024** |
| **አንድ-ለ-አንድ ለቴክኒካዊ ድጋፍ የተወሰነ ጊዜ** | **መጋቢት 28 ቀን 2024፣ እስከ ግንቦት 7 ቀን 2024 መካከል፣ በቀጠሮ** |
| **የጥያቄ እና መልስ ክፍለ ጊዜ** | **መጋቢት 28 ቀን 2024፣ እስከ ግንቦት 7 ቀን 2024 መካከል** |
| **ለውሳኔ የሚቀርቡ ሀሳቦች እስከ** | **ግንቦት 9 ቀን 2024፣ 11:59 ሌሊት ድረስ** |

***ዕለተ ቀኖች እና ጊዜያቶች ሊለወጡ ይችላሉ**

## ለውሳኔ የቀረቡ ሀሳቦች ማህበረሰብን መሠረት ላደረጉ የቴክኒካል ድጋፍ

ልምድ ያላቸው ማህበረሰብን መሠረት ያደረጉ አማካሪዎች ለውሳኔ የቀረቡ ሃሳባቸውን አቅራቢዎች እንዲያዳብሩ ለመርዳት ነፃ፣ ቀጥተኛ ቴክኒካዊ ድጋፍ (TA) አለ። ለውሳኔ ያለዎት ሀሳብዎን ልማት ለመደገፍ፣ ከዚህ ለውሳኔ የቀረበ ሀሳብ ጥያቄ RFP ቅድሚያዎቹ ጋር የሚስማማ እና የ RFP ቴክኒካዊ መመሪያን ለመገምገም የቴክኒካዊ ድጋፍን እንዲጠቀሙ እጅግ አጥብቀን እናበረታታለን። የቴክኒካዊ ድጋፍን እርዳታ ለመጠቀም፣ እባክዎን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማንኛቸውንም አማካሪዎች ለማግኘት/ ለመድረስ ነፃነት ይሰማዎት።

| ቴክኒካዊ ድጋፍ (TA) አቅራቢ | ዳራ እና ግንኙነት |
|---|---|
| ካትሪን ቬሬንቲ (Catherine Verrenti) | ካትሪን ቬሬንቲ በማህበረሰቡ ውስጥ በጥልቀት የተካተቱ ማህበረሰብን መሠረት ያደረጉ ድርጅቶችን (CBOs) ለመደገፍ እድል በማግኘታቸው በጣም ተደስተዋል። በጎረቤት ቤት እና የወጣትእንክብካቤ (Neighborhood House and YouthCare)ን ጨምሮ፣ በተግባር ከሃያ አመታት ያገኘችውን ልምድ፣ ክህሎቶች እና ግንዛቤዎችን ታቀርባለች። ይህ እውቀት የገንዘብ ስጦታ ማዳበርን እና ሰፋ ያለ ባህላዊ ምላሽ ሰጪ የወጣቶች እድገትን፣ የቤተሰብ ድጋፍን፣ ከትምህርት ቤት ውጭ ጊዜ፣ የጉዳይ አስተዳደርን እና ቤት አልባ ፕሮግራሞችን ሥራ ማካሄድ ያጠቃልላል።<br>ያግኙን: catherine@verrenticonsulting.com |
| ሀሰን ዋርዴር | ሀሰን ዋርዴሬ በፕሮጀክት አስተዳደር፣ በትክክለኛ የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ በአቅም ግንባታ፣ በለውጥ አስተዳደር፣ በስልታዊ እቅድ ማውጣት እና አጋርነት፣ በቴክኒካዊ ድጋፍ፣ ወዘተ ልዩ ችሎታ አለው። |

Seattle Department of Education & Early Learning

| | |
|---|---|
| (Hassan Wardere) | ሃሰን የስልታዊ ሀሳቦችን ለማዳበር ድጋፍ ሲሰጥ፣ የተሳካ ንድፎችን እና የፈጠራ፣ ለደንበኞች የተበጁ፣ በፍትሃዊ እኩልነት ላይ የተመሰረቱ ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን በማዋሃድ የቤት ውስጥ ባህሎችን ዋጋ በመስጠት ልዩ የሆነ ስልት ይጠቀማል። እንዲሁም የአዲስ ሰፋሪ እና የስደተኛ ቤተሰቦችን ከሚያገለግሉ ማህበረሰብን መሠረት ካደረጉ ድርጅቶች (CBOs) ጋር በመስራት ደግሞ ሰፊ ልምድ አለው።<br>ያግኙ: projects@bulleconsulting.com |

## የቋንቋ ድጋፎች

ተጨማሪ የቋንቋ ድጋፍ ከፈለጉ፣ የትምህርት እና የቅድመ ትምህርት መማሪያ መምሪያ (DEEL) እርዳታ ሊሰጥ ይችላል። እባክዎን የ **DEEL የገንዘብ ድጋፍን** በ**deelfunding@seattle.gov** ያግኙ።

## ተጨማሪ መረጃ

የገንዘብ ስጦታ ሙሉ ዝርዝሮች ከቅድመ ወሊድ እስከ ሶስት ዓመት የማህበረሰብ የስጦታ ገንዘብ ፕሮግራም ለውሳኔ የቀረቡ ሀሳቦች ጥያቄ (Prenatal to Three Community Grant Program Request for Proposal) ውስጥ በዋና ዋና ነጥቦች ይገኛሉ። ለዚህ የገንዘብ ስጦታ ፕሮግራም ሁሉም መረጃ እና የማመልከቻ ሰነዶች በ DEEL የገንዘብ ድጋፍ እድሎች ድህረ-ገጽ ላይ ይገኛሉ: http://www.seattle.gov/education/for-providers/funding-opportunities